የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 8
ADDIS ABABA 4th December, 2012

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸፪/፪ሺ፭ ዓ.ም.
የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………ገፅ ፮ሺ፮፻፸፩

CONTENTS

Regulation No. 272/2012
Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority Establishment Council of Ministers Regulation ……………………………….. Page 6671

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፪/፪ሺ፭

## የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭ እና አንቀጽ ፴፬ መሠረት ይህንን ደንብ አዉጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፪/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

፩/ "አዋጅ" ማለት የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፯፻፳፰/፪ሺ፬ ነው፤

፪/ "የእንስሳት መድኃኒት"፣ "መኖ" እና "የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገር" በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተሰጣቸዉን ትርጉም ይይዛሉ፤

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 272/2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF VETERINARY DRUG AND ANIMAL FEED ADMINISTRATION AND CONTROL AUTHORITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Authority Establishment Council of Ministers Regulation No. 272/2012".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Veterinary Drug and Animal Feed Administration and Control Proclamation No. 728/2011;

2/ "veterinary drug", "feed" and "feed additives" shall have the meanings assigned to them under Article 2 of the Proclamation;

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫/ "ሚኒስቴር" ወይም "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፬/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባንና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፭/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፮/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል።

፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለስልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ባለስልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የባለስልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭. <u>ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ ዓላማ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግና ጤናማ የእንስሳት ምርት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዲቀርብ ማስቻል ይሆናል።

፮. <u>የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በአዋጁ አንቀጽ ፳ እና አግባብ ባላቸው ሌሎች አንቀጾች የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፤

ለ) በመንግሥት በሚወሰን ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

ሐ) የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በራሱ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

መ) ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

፪/ ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል አግባብ ላላቸዉ የክልል አካላት ዉክልና ሊሰጥ ይችላል።

3/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Agriculture, respectively;

4/ "Region" means any region referred to under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

5/ "person" means any natural or juridical person;

6/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Establishment</u>

1/ The Veterinary Drug and Feed Administration and Control Authority (hereinafter the "Authority") is hereby established as an autonomous federal government organ having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Ministry.

4. <u>Head Office</u>

The head office of the Authority shall be in Addis Ababa and it may have branch offices elsewhere, as necessary.

5. <u>Objective</u>

The objective of the Authority shall be to ensure improvement of animal productivity and availability of wholesome animal products to the consumers.

6. <u>Powers and Duties of the Authority</u>

1/ The Authority shall have the powers and duties to:

a) exercise the powers and duties granted to it by Article 20 and other relevant provisions of the Proclamation;

b) collect service fee in accordance with the rate determined by the government;

c) own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

d) perform such other related activities as may be necessary for the attainment of its objective.

2/ The Authority may, where it finds it necessary, delegate part of its powers and duties to appropriate regional organs.

፯. **የባለሥልጣኑ አቋም**

ባለሥልጣኑ፦

፩/ አማካሪ ቦርድ፤

፪/ በመንግስት የሚሾሙ አንድ ዋና ዳይሬክተርና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች፤ እና

፫/ አስፈላጊዉ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

፰. **የአማካሪ ቦርዱ አባላት**

አማካሪ ቦርዱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

፩/ በሚኒስትሩ የሚሰየም ኃላፊ...............ሰብሳቢ፤

፪/ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ......... አባል፤

፫/ አግባብ ካላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የሙያ ማኅበራት እና የተጠቃሚዎች ማኅበራት ተውጣጥተው በሚኒስትሩ የሚሰየሙና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ሰዎች......አባላት።

፱. **የአማካሪ ቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት**

አማካሪ ቦርዱ፦

፩/ የእንስሳት መድኃኒት ደህንነትና ፈዋሽነት እና የመኖ የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሥርዓትን በሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ዝግጅትና አፈጻጸም፤

፪/ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ወይም የጥራት ደረጃውን ያላሟሉ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መኖዎችና የመኖ ተጨማሪ ንጥረ ነገሮች በአግባቡ በሚወገዱበት ሥርዓት፤ እና

፫/ የእንስሳት መድኃኒትና መኖን በሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አተገባበር፤

ላይ የማማከር ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።

፲. **የአማካሪ ቦርዱ ስብሰባዎች**

፩/ አማካሪ ቦርዱ ለሥራው ባስፈለገ መጠን ይሰበሰባል።

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የአማካሪ ቦርዱ አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

፫/ የአማካሪ ቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው ውሳኔ ያልፋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው አማካሪ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

7. **Organization of the Authority**

The Authority shall have:

1/ an Advisory Board;

2/ a Director General and, as may be necessary, Deputy Director Generals to be appointed by the government; and

3/ the necessary staff.

8. **Members of the Advisory Board**

The Advisory Board shall have the following members:

1/ an officer to be designated by the Minister..........................................................Chairperson;

2/ a representative of the Ministry of Health...........................................................Member;

3/ persons to be drawn from the appropriate higher education institutions, professional associations and consumers associations and to be designated by the Minister and the number of which shall be determined as may be necessary ...........Members.

9. **Duties and Responsibilities of the Advisory Board**

The Advisory Board shall have the duties and responsibilities to provide advice on:

1/ the formulation and implementation of policies, strategies and guidelines for ensuring the safety and efficacy of veterinary drugs and quality standards of feed;

2/ proper disposal system for expired and substandard veterinary drugs, feed and feed additives;

3/ the implementation of international agreements concerning veterinary drugs and feed.

10. **Meetings of the Advisory Board**

1/ The Advisory Board shall meet as frequently as its functions require.

2/ There shall be a quorum where more than half of the members of the Advisory Board are present at any meeting.

3/ Decisions of the Advisory Board shall be passed by majority vote; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Advisory Board may adopt its own rules of procedure.

፲፩. **የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር**

፩/ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ አገላለጽ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ፡-

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፲፪. **በጀት**

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

፲፫. **ስለሂሣብ መዛግብት**

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

፲፬. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ህዳር ፳፭ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

11. **Powers and Duties of the Director General**

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and shall, subject to the general directions of the Ministry, direct and administer the activities of the Authority.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Authority stated under Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees of the Authority in accordance with the federal civil service laws;

c) prepare and submit to the Ministry the work program and budget of the Authority, and implement same upon approval;

d) effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Authority;

e) represent the Authority in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry the performance and financial reports of the Authority.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officers and staff of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

12. **Budget**

The budget of the Authority shall be allocated by the government.

13. **Books of Accounts**

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor assigned by the Auditor General.

14. **Effective Date**

This Regulation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Abab., this 4th day of December, 2012.

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ